# የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎችን እንደ ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች መሰየሚያ መመሪያ ቁጥር 934/2015

ሕዳር  2015 ዓ.ም

የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት

<u>**የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎችን እንደ ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች መሰየሚያ መመሪያ ቁጥር 934/2015**</u>

የባለሞተር ተሽከርካሪዎች የንግድ ሥርዓት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብንና ሽብርተኝነን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎችን ለሚፈጽሙ ወንጀለኞች መደበቂያ ዘርፍ መሆኑን ጥናቶች የሚያረጋግጡ በመሆኑ፤

የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎችን ስራ ተጠያቂነትና ግልጸኝነትን ለማረጋገጥ አስቻይ ከባቢ በመፍጠር በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብንና ሽብርተኝነን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎችን መከላከልና መቆጣጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብንና ሽብርተኝነን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎችን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አኳያ የባለሞተር ተሽከርካሪዎች የንግድ ዘርፍን የሚመራ የህግ ማዕቀፍ አስፈላጊነቱ የታመነበት በመሆኑ፤

የባለሞተር ተሽከርካሪዎች የንግድ ዘርፍ ውስጥ የሚገኙ ባለድርሻ አካላት በአዋጁና በመመሪያው ውስጥ የተደነገጉ ግዴታዎቻቸውን እንዲወጡ የውስጥ የአሰራር ስርዓቶች እና ማኑዋሎች እንዲኖራቸውና ስጋቶችን በራሳቸው አቅም እንዲለዩ ለማድረግ አቅማቸውን ማጎልበት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች ደንበኞቻቸውን እንዲለዩ ለማስቻልና በዚህም የወንጀሉቹ መፈጸሚያ መሳሪያ እንዳይሆኑ መጠበቅ/መከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፤

በአዋጅ ቁጥር 780/2005 አንቀጽ 2(10) (ሠ) እና በአንቀጽ 54(2) መሰረት የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ**

**ይህ መመሪያ የሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎችን እንደ ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎች መሰየሚያ መመሪያ ቁጥር 934/2015 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል**

**አንቀጽ 2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1. **"የባለሞተር ተሽከርካሪ**« ማለት በመካኒካል ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል እየተንቀሳቀሰ የሚሄድ ተሽከርካሪ ሆኖ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ባለሞተር ብስክሌት፣ የግል አውቶሞቢል፣ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ጎታች መኪና እና ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያን ያጠቃልላል፤
2. **"ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ**« ማለት ሰውን ወይም ዕቃን በመንገድ ላይ እንዲያመላልስ ሆኖ የተሠራ ተሽከርካሪ ሳይሆን ለእርሻ፣ ለአትክልት፣ ለከብት እርባታ፣ ለመንገድ፣ ለሕንጻ፣ ለቁፋሮ ወይም ለማንኛውም ተመሳሳይ ሌላ ሥራ የተሠራ ወይም ለዚሁ ጉዳይ እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤
3. **"የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች**« ማለት የባለሞተር ተሽከርካሪዎችን የሚያመርቱ፣ ከውጭ ሀገራት የሚያስመጡ፣ ወደ ውጭ ሀገራት የሚልኩ፣ የሚያከፋፍሉ፣ የሚቸረችሩ፣ የሚያከራዩ፣ ለሽያጭ የሚደልሉ እና ከዘርፉ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ያጠቃልላል፤
4. **"ተጠቃሚ የሚሆን ባለቤት**« ማለት ደንበኛን ወይም አንድን ሂሳብ በፍጹም ባለቤትነት የሚይዝ ወይም የሚቆጣጠር ግለሰብ፣ ግብይት በስሙ የሚካሄድለት ሰው ወይም አንድን በህግ የሰውነት መብት የተሰጠውን አካል ለመቆጣጠር ፍጹም ስልጣን ያለው ሰው ነው፤
5. **"ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**" ማለት የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎችን እንዲቆጣጠር በህግ ስልጣን የተሰጠው የመንግስት አካል ሆኖ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚኒስቴር፡ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፤ አግባብነት ያላቸውን የክልል እና የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቢሮዎችን ያካትታል፤
6. "**አዋጅ**« ማለት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 780/2005 ማለት ነው፤
7. "**መመሪያ**« ማለት ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎች የጸረ-በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነን በገንዘብ መርዳትን መከላከል ኮምፕሊያንስ መመሪያ ቁጥር 02/2008 ማለት ነው፤
8. "**አገልግሎት**« ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 490/2014 የተቋቋመው የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ነው፤

9. “ሰው“ ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
10. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፤
11. በአዋጁ አንቀጽ 2 እንዲሁም በመመሪያው አንቀጽ 2 ላይ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 3. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሰሩ የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 4. መሰየም**

የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች በአዋጁ አንቀጽ 2(10) (ሠ) መሠረት “ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎች“ ተብለው ተሰይመዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነን በገንዘብ መርዳትን ስለመከላከልና ስለመቆጣጠር

**አንቀጽ 5. የውስጥ የመከላከል ፕሮግራም**

1. የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች አዋጁን፣ መመሪያውን እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ህጎችን በተከተለ አግባብ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብንና ሽብርተኝነን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎችን የመከላከል የዉስጥ ፖሊሲዎችና ቁጥጥሮች መዘርጋትና በስራ ላይ ማዋል እንዲሁም የእነዚህን ፖሊሲዎችና ቁጥጥሮች አተገባበር መከታተልና አስፈላጊ ሲሆንም ማጠናከር አለባቸዉ።

2. በንዑስ አንቀጽ አንድ ላይ በተደነገገው መሰረት የሚዘረጉና የሚተገበሩት ተገቢነት ያላቸው ፖሊሲ፣ የአሰራር ስርዓቶች፣ የአሰራር ሂደቶች እና የቁጥጥር ስርዓቶች የሚከተሉትን የሚያካትት ይሆናል፡-

    ሀ. በጽሁፍ የሰፈረ የተገዥነት (ኮምፕሊያንስ) ፖሊሲ እና የውስጥ አሰራር ስነ-ስርዓቶስ

    ለ. የተገዥነት (ኮምፕሊያንስ) ባለሙያ መሾም

    ሐ. ስልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጥ

    መ. የሰራተኞች ማንነትን ማጣራት

    ሠ. የተገዥነት ስርዓት ጥራትን ለማረጋገጥ ገለልተኛ የሆነ የምዘና ስርዓት መኖር

**አንቀጽ 6. የስጋት ዳሰሳ**

1. የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች ከደንበኞቻቸው፣ ከንግዳቸው፣ ከምርትና አገልግሎታቸው፣ ከአካባቢያዊ ተጋላጭነት፣ ከንግድ እንቅስቃሴ፣ ምርትን ወይም አገልግሎትን ከማቅረቢያ ስርዓት፣ ከግብይቱ መጠን እንዲሁም ከሌሎች ሁነቶች አንጻር በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብንና ሽብርተኝነን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎች ስመለየት፣ ስመፈተሽ እና ስመረዳት የስጋት ዳሰሳ ጥናት የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

2. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብን ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመደገፍ ወንጀሎች የተጋላጭነት የስጋት ዳሰሳ በሚደረግበት ወቅት የሚከተሉትን ተግባራት መከናወን አለባቸው፤

   ሀ. የስጋት ዳሰሳቸውን መዝግቦ መያዝ፤

   ለ. የጠቅላላ የተጋላጭነት ስጋት ደረጃ ምን ያህል እንደሆነ ከመወሰን በፊት እና መደረግ ያለበትን አግባብነት ያለውን የስጋት መቀነሻ ዘዴዎችንና ደረጃ ከመወሰን በፊት ሁሉን የስጋት መንስኤዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት፤

   ሐ. የስጋት ዳሰሳውን ወቅታዊ ማድረግ፤ እና

   መ. አገልግሎቱ በሚያቀርበው የመረጃ መሳኪያ ዘዴ የስጋት ዳሰሳ መረጃዎችን ስአገልግሎቱ ማቅረብ፡፡

**አንቀጽ 7. የደንበኛን ማንነት ስማወቅ የሚያስችሉ የጥንቃቄ እርምጃዎች**

1. የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች የደንበኞቻቸውን ማንነት ስመለየትና ስማረጋገጥ የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓቶችን የማዘጋጀት ግዴታ አለባቸው፡፡ ደንበኞቻቸውን ማንነታቸውን የሚገልጽ የመታወቂያ ሰነዶች እንዲያቀርቡ ማድረግ አለባቸው፤ ደንበኞቻቸው የሚደቅኑትን የስጋት ልክ ስመለየት ያስችሳቸው ዘንድ ከደንበኞቻቸው አስፈሳጊ መረጃዎችን መቀበል አለባቸው፡፡

2. የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች የሚከተሉትን የደንበኛን ማንነት ስማወቅ የሚያስችሉ የጥንቃቄ እርምጃ መርሆችን/ደረጃዎችን መተግበር አለባቸው፡-

   ሀ. ተዓማኒ፣ ከገለልተኛ ምንጭ የተገኙ ሰነዶችን፣ ዳታዎችን ወይም መረጃዎችን በመጠቀም የደንበኞችን ማንነት መለየትና ማረጋገጥ፤

   ለ. ሌሳ ደንበኛን በመወከል የሚመጣ ሰውን ስልጣን ስለመኖሩ ማረጋገጥ፤ እንዲሁም የወካዩን ግለሰብ ማንነት መለየትና ማረጋገጥ፤

ሐ. በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸውን ደንበኞችን የባለቤትነትና የአመራር መዋቅራቸው ለመረዳት እንዲሁም እንዚህን ደንበኞች በዋናነት በባለቤትነት ወይም በአመራርነት የሚቆጣጠሩ ግለሰቦችን ለመለየት የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸውን እርምጃዎች መውሰድ፤

መ. ተጠቃሚ የሚሆኑትን ባለቤቶች ማንነት መለየትን እና ይህንኑ ለማረጋገጥ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድን፤ ገለልተኛ የሆኑ ምንጮችን መሰረት ያደረጉ መረጃዎችንና ዳታዎችን መሰረት በማድረግ ተጠቃሚ የሚሆኑትን ባለቤቶች ማንነት ማወቅ፤

ሠ. ከደንበኛው ጋር በሚካሄደው ቀጣይነት ባለው የንግድ ግንኙነቱ ውስጥ ቀጣይነት ያለው የደንበኛን ማንነት የመለየት ተግባርንን ማከናወን፡፡

3. የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች የደንበኛን ማንነት ለማወቅ የሚያስችሉ የጥንቃቄ እርምጃዎች መውሰድ ያለባቸው፡-

ሀ. የንግድ ግንኙነቱን በሚመሰረትበት ወቅት፤

ለ. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብንና ሽብርተኝነን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎች ስለመፈጸማቸው ጥርጣሬ ሲኖር፤ እና

ሐ. አስቀድሞ ስለተያዘው የደንበኛው ማንነት መለያ መረጃዎች ላይ ተዓማኒነት ወይም በቂ መሆን ላይ ነጋዴው ጥርጣሬ ሲኖረው፤

4. የደንበኛን ማንነት ለመለየትና ለማረጋገጥ የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች ሲይዙ የሚገባቸውን መረጃና የማንነት መለያ ሰነዶችን በተመለከተ ዝርዝራቸውን በመመሪያው ከአንቀጽ 15 - አንቀጽ 17 የተመለከቱትን ይሆናል፡፡

5. ማንነትን የመለየትና የማረጋገጥ የጊዜ ወሰንን በተመለከተ በመመሪያው አንቀጽ 18 ላይ የተመለከተው ድንጋጌ ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

**አንቀጽ 8. የተጠናከሩ የጥንቃቄ እርምጃዎች**

የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች የሚከተሉትን መረጃዎች ካገኙ የተጠናከሩ የጥንቃቄ እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡ እንዚህም፡-

ሀ. ደንበኛው በሰጣቸው መረጃዎች ወይንም ሰነዶች ወይንም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ተቋም ባለቤትነት ትክክለኛነት ላይ ጥርጣሬ ከተፈጠረ፤

ለ. መረጃው ደንበኛው ከዝቅተኛ ወይንም መካከለኛ የስጋት ደረጃ ወደ ከፍተኛ ስጋት ደረጃ መደብ ለማስመደብ በቂ ምክንያት ሆኖ ሲገኝ፤

ሐ. አግባብነት ባላቸው አለም ዓቀፍ ተቋማት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብንና ሽብርተኝነን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎች ከፍተኛ የሆነ ተጋላጭነት አለባቸው ተብለው በተገለጹ ሀገራት ከሚኖሩ ሰዎች ጋር የንግድ ግንኙነት ሲመሰርቱ፤

## አንቀጽ 9. ከፍተኛ ስጋት ያለባቸው ደንበኞች

1. ከፍተኛ ስጋት ያለባቸው ደንበኞች የሚባሉት፡-

   ሀ. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብንና ሽብርተኝነን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎች ለመከላከልና ለመቆጣጠር በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የተዘረጉ መመዘኛዎችን በበቂ ሁኔታ እንደማያሟሉ ከታወቁ ሀገራት የሚመጡ ደንበኞች፤

   ለ. አስፈላጊ ያልሆነ ውስብስብ ወይም ግልጽ ያልሆነ ተጠቃሚ የሚሆን ባለቤት መዋቅር ያለው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ደንበኞች፤

   ሐ. ለፖለቲካ ተጽኖ የተጋለጠ ሰው የሆነ ደንበኛ፤

   መ. ለህዝብ ክፍት በሆኑ የመረጃ ምንጮች መሰረት ባህሪያቸው/ ሥነ-ምግባራቸው አጠራጣሪ የሆኑ ሰዎች፤

   ሠ. በሀገሪቱ ውስጥ ስራ የሚሰሩ ዋና መኖሪያቸው ከሀገር ውጪ ያደረጉ ደንበኞች፤

   ረ. ታዓማኒነት ባላቸው ምንጮች ከፍተኛ የሆነ ሙስና፤ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር፤ የአደንዛዥ ዕፅ ንግድ እና ሌሎች ከባባድ ወንጀሎች ይፈጸምባቸዋል ተብለው ከተለዩ ሀገራት ጋር ግንኙነት ያላቸው ደንበኞች፤

   ሰ. ታዓማኒነት ካላቸው ምንጮች ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከሚረዱ ወይም ከሚደግፉ ወይም የተሰየሙ የአሸባሪ ድርጅቶች የሚንቀሳቀሱባቸው ሀገራት ወይም አካባቢዎች የሚገኙ ደንበኞች ናቸው፡፡

2. የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች ከፍተኛ ስጋት ካለባቸው ደንበኞች ጋር የስራ ግንኙነት ሲፈጥሩ ወይም አስቀድሞ የነበረ ደንበኛቸው በንዑስ አንቀጽ አንድ ስር በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ምክንያት ወደ ከፍተኛ ስጋት ያለባቸው ደንበኞች ዝርዝር ውስጥ የሚካተት ሆኖ ከተገኘ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ላይ በተደነገገው ድንጋጌ መሰረት የተጠናከሩ የጥንቃቄ እርምጃዎች የመውሰድ ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ 10. የጥርጣሬ ግብይቶችን የማሳወቅ ግዴታ

1. የጥርጣሬ ግብይት ማለት ግብይት የፈጸመ ወይም ግብይት ለማድረግ የተፈጸመ ሙከራ ሆኖ የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች ወይም ባለሙያው ለግብይት የቀረበለት ገንዘብ የወንጀል ፍሬ ስለመሆኑ፤ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያዘ ወይም የተገናኘ ወይም ለዚሁ ተግባር ሊውል የሚችል ስለመሆኑ ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖረው እና ማንኛውም አይነት አጠራጣሪ የሆነ ህገ ወጥ ግብይት መፈጸም ወይም ለህገወጥ ተግባር አላማ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ለመተላለፍ መሞከር ማለት ነው፡፡

2. የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች ከደንበኞቸው ጋር በሚያደርጉት የግብይት ሂደት ጥርጣሬ ወይም ለመጠርጠር ምክንያታዊ መሰረት ሲኖር ግብይቱን ለአገልግሎቱ ወዲያውኑ የማሳወቅ ግድታ አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 11. የጥርጣሬ ግብይት ጠቋሚዎች**

1. ጠቅላላ ጠቋሚ ሁነቶች

ሀ. ግብርን ለመሰወር በማሰብ፣ ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸውን ባለሞተር ተሽከርካሪዎች መግዛትና አነስተኛ ግብር መክፈል

ለ. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ ለማቅረብ በማሰብ ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን በከፍተኛ ዋጋ መሸጥና ከፍተኛ ግብርን መክፈል

ሐ. በህገወጥ መንገድ የተገኘውን ገንዘብ ለመደበቅ በማሰብ የሌላሰውን ባለሞተር ተሽከርካሪ የገዛ እና ወንጀሉን የፈጸመውን ግለሰብ ማንነት የደበቀ

መ. ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ሽፋን ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሬ ከሀገር ውጭ እንዲሳክ ማድረግ፡፡

2. ልዩ ጠቋሚ ሁነቶች

ሀ. ደምበኛው ከፍተኛ በሆነ የገንዘብ መጠን ባለሞተር ተሽከርካሪን ለመግዛት መሞከር፤

ለ. ደንበኛው ግብይቱን ለማጠናቀቅ የሚያስችሉ ማንነቱን የሚገልጹ ሰነዶችን ለማቅረብ በተጠየቀ ጊዜ የተቃወመ እንደሆነ፤

ሐ. ደንበኛው ከፍተኛ የሆነ ቅድመክፍያ በጥሬ ገንዘብ የከፈለ እንደሆነ፤

መ. ግዥው የሚከናወነው ግዥውን ለመፈጸም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ አቅም በሌላቸው ግለሰቦች ስም መሆኑ፤

ሠ. በቼክ ክፍያው እንዲመለስላቸው፤ ግብይቱ ሲጠናቀቅ ጥቂት ሂደቶች ሲቀሩት የግዥ ትዕዛዝን መሰረዝ፤

ረ. ደንበኛው ባለሞተር ተሽከርካሪውን ያለምንም ምክንያታዊ ምርመራ ግዢ የፈጸመ እንደሆነ፤

ሰ. ደንበኛው በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዛት ያላቸውን የባለሞተር ተሽከርካሪ ግዥ የፈጸመ እንደሆነ እና ስለተሽከርካሪው አይነት፣ ዋጋ፣ ይዞታ፣ወዘተ ጉዳዮች አስፈላጊው አትኩሮት ያልሰጠው እንደሆነ፤

ሸ. ደንበኛው የወንጀል የኃላ ታሪክ ያለው መሆኑ የሚታወቅ ከሆነ፤

ቀ. ደንበኛው የተለያ ስሞችን የተጠቀመ ከሆነ ወይም በተለያዩ ስሞች የተዘጋጁ የማንነት መግጫ ሰነዶችን ያቀረበ እንደሆነ፤

በ. ደንበኛው ከባለሞተር ተሽከርካሪው ግዥ ጋር በተገናኘ በማንኛውም ሰነድ ላይ የራሱን/የራሷን ስም ማስመዝገብ ማይፈልግ/የማትፈልግ ከሆነ፤

ተ. ግዥው ደንበኛው ከገለጸው ወይም ከሚታወቀው ሙያው ወይም ከገቢው አንጻር የማይመጣጠን ከሆነ፤

**አንቀጽ 12. የመዝገብ አያያዝ**

1. የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች በዝርዝር መዝገቦችን፣ ሰነዶችን፣ መረጃዎችን እና ስታትስቲኮችን በተደራጀና ሚስጥራዊ በሆነ መልኩ የመያዝ ግዴታ አለባቸው፡፡

   ሀ. ሁሉንም ግብይቶችን

   ለ. የደንበኛን ማንነት ለማወቅ የሚያስችሉ የጥንቃቄ እርምጃዎች ሂደት የተገኙ መረጃዎች

   ሐ. መዘገቦችንና የንግድ ደብዳቤዎችን

   መ. የጥርጣሬ ግብይት ሪፖርቶች/ የገንዘብ ግብይት ሪፖርቶች

   ሠ. የስጋት ዳሰሳ ጥናቶችን እና የስጋት ማቅለያ እርምጃዎች፡፡

2. ግብይቱ ከተከናወነበት እለት አንስቶ ለአስር (10) ዓመታት ወይም የንግድ ግንኙነቱ እስከቀጠለበት ጊዜ ድረስ መረጃዎቹን መያዝና ደህንነቱ በተጠበቀ አኳኃን የማከማቸት ግዴታ አለባቸው፡፡

3. መረጃዎቹ ተደራሽ በሆነ አግባብ እና በተቆጣጣሪ አካላት በማንኛውም ጊዜ ለመፈተሽ በሚያስችል መልኩ ተሞልቶ መያዝ አለበት፡፡

**አንቀጽ 13. መረጃን አሳልፎ መስጠትን ስለመከላከል**

1. የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች ወይም ማንኛውም የድርጅቱ ዳይሬክተር፣ ኃላፊ ወይም ተቀጣሪ ሰራተኛ የጥርጣሬ ግብይት ሪፖርት የተደረገ ወይም ሪፖርት ሲደረግ መሆኑን፣ የሪፖርቱን ይዘት፤ ወይም ከሪፖርቱ ጋር የተገናኘ ማንኛውንም ዓይነት መረጃ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፤ በማንኛውም ሁኔታ ወይም መንገድ ለማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ወይም ሚዲያ መግለጽ የተከለከለ ነው፡፡

2. የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች ሪፖርት የሚደረጉት መረጃዎችና ዳታዎች ባልተፈቀደላቸው ሰዎች ተደራሽ እንዳይሆኑ አግባብነት ያላቸውን እርምጃዎች የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡

3. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉትን ግዴታዎች የተላለፈ የሚመለከተው ዳይሬክተር፤ ኃላፊ ወይም ተቀጣሪ ሰራተኛ በአዋጁ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 14. ተፈጻሚነት ያላቸው ሕጎች

ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎች የጸረ-በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነን በገንዘብ መርዳትን መከላከል ኮምፕሊያንስ መመሪያ ቁጥር 02/2008 በዚህ መመሪያ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

### አንቀጽ 15. አስተዳደራዊ እና የወንጀል ተጠያቂነት

1. የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎችን የተላለፈ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች መሰረት በወንጀል የሚጠየቅ ይሆናል፡፡

2. የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎችን የሚጥስ ማንኛውም ሰው የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎችን ስመቆጣጠር፣ ስመከታተል፤ ፍቃድ ስመስጠት ወይም ሌላ ተመሳሳይ ስልጣን በተሰጣቸው አግባበነት ባላቸው ተቆጣጣሪ ባለስጣን መስሪያ ቤቶች ስሚጣሉ አስተዳደራዊ ቅጣቶች ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል፡፡

### አንቀጽ 16. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በአገልግሎቱ ጸድቆ በፍትህ ሚኒስቴር ድህረ-ገጽ ላይ ከተመዘገበ በኋላ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ሕዳር 2015 ዓ.ም

**አቶ ቴዎድሮስ በቀለ ገርቢ**

**ዋና ዳይሬክተር**

**የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት**